## የማቴዎስ ፩ ሴቶች

# ሩት

የጥናት መምሪያ

Selah
PAUSE • REFLECT



# መግቢያ

በማቴዎስ ፩ ውስጥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ የአምስት ሴቶችን ስም እናያለን። ለብዙዎቻችን የዘር ሐረግ መቁጠር ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን አብልጠን የምንወደው አካል ላይሆን ይችላል። አንዳንዶቻችን ከነጭራሹ ልንዘለው እንችላለን። ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘሩት በእያንዳንዱ የዘር ሐረጎች ውስጥ ትኩረትን የሚስቡ አስደናቂ ነገሮችን እናያለን፣ ማቴዎስ ፩ም እንዲሁ ነው።

የሴቶች ወይም የእናቶች ስም በአይሁድ የዘር ሐረግ ውስጥ በተለምዶ አይጠቀሱም። በእውነቱ በአይሁድ ታሪክ ዝና የነበራቸውን ትውልዶች ብቻ በመጥቀስ፣ ሌሎችን በመዝለል የዘር ሐረጎችን በአጭሩ የሚጽፉ ሰዎች ስለነበሩ፣ በዘር ሐረግ ውስጥ መጠቀስ ራሱ በጣም ትልቅ ክብር ነበር። ይህንን ስናስብ እነዚህ አምስት ሴቶች ማለትም ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት፣ ቤርሳቤህ እና የኢየሱስ እናት ማርያምን ማቴዎስ መጥቀሱ በእርግጥ ሊያስደንቀን ይጀምራል።

እነዚህ አምስት ሴቶች ሕይወታቸው ሲጠና ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ እና ስለ እለት ተእለት ሕይወት የሚነግረን ነገር አለ።

# ስለ ጥናት መምሪያው

የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ስንፈልግ መንፈስ ቅዱስ ዋና አስተማሪያችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢየሱስ “መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል” ይለናል (ዮሐንስ 14፥26)። በጥናታችን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን፣ እንዲለውጠን ከመጠየቅ ባሻገር የሚከተሉትን ይዘው መዘጋጀት ጠቃሚ  ነው ብለን እናስባለን።

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ማስታወሻ ደብተር (ሐሳብዎን ለማስፈሪያ ቦታ ስላለው ይህንን መምሪያ አትመው በማውጣት መጠቀም ይችላሉ)
- በመጽሐፍ ቅዱስዎ ወይም በማስታወሻዎ ውስጥ ለመጻፍ ቀለም ያላቸው እስኪብርቶዎች ወይም እርሳሶች

በዚህ ጥናት ውስጥ ሁሉ ራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች እየጠየቁ ይሂዱ፥

- ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ልብ፣ መንገዶች፣ እና ባሕርይ ምን ይነግረኛል?
- ይህ ክፍል ወደ ኢየሱስ እና ወደ ወንጌል እንዴት ይጠቁማል?
- ልከተለው ወይም ላስወግደው የሚገባ ምሳሌ አለ? ከሆነስ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ወይም ምላሽ መስጠት አለብኝ?

# ማውጫ


ምዕራፍ 1

ምዕራፍ 2

ምዕራፍ 3

ምዕራፍ 4



© 2020 by Selah Ministries



Published by Selah Ministries
P.O. Box 479, Addis Ababa, Ethiopia

Published in Addis Ababa, Ethiopia


All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form without permission from the publisher, except in the case of brief quotations embodied in other works or reviews.

All Scripture quotations are from the NASV Amharic Bible (Holy Bible, New Amharic Standard Version (Addisu Medebegna Tirgum)) Copyright © 2001 by Biblica, Inc.®
All rights reserved worldwide.



Illustrations
Front cover: Yikunoamlak Ayalew
Back cover: Ammanuel Anbessie

ተጓዳኙን የጥናት ቪዲዮ መመልከት ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ቪዲዮውን ከዚህ በታች ያለውን ምስል በመንካት ወይም በድህረ-ገፃችን www.selahethiopia.org/ruth ያገኙታል።




# ሩት 1

መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን፣ በምድሪቱ ላይ ራብ ሆነ፤ አንድ ሰው በይሁዳ ከምትገኘው ከቤተ ልሔም ሚስቱንና ሁለቱን ወንዶች ልጆቹን ይዞ፣ ለተወሰነ ጊዜ ለመኖር ወደ ሞዓብ አገር ሄደ። የሰውየው ስም አቤሜሌክ፣ የሚስቱ ኑኃሚን፣ የሁለቱም ወንዶች ልጆቹ ስም መሐሎንና ኬሌዎን ነበሩ። እነርሱም የይሁዳ ቤተ ልሔም ኤፍራታውያን ሲሆኑ፣ ወደ ሞዓብ አገር ሄደው በዚያ ኖሩ።

የኑኃሚን ባል አቤሜሌክ ሞተ፤ ኑኃሚንም፣ ከሁለት ልጆቿ ጋር ብቻዋን ቀረች። ልጆቿም ዖርፋና ሩት የተባሉ የሞዓብ ሴቶችን አገቡ፤ በዚያም ዐሥር ዓመት ያህል ከኖሩ በኋላ፣ መሐሎንና ኬሌዎን ሁለቱም ሞቱ፤ ኑኃሚንም ሁለት ልጆቿንና ባሏን አጥታ ብቻዋን ቀረች።

እርሷም በሞዓብ ሳለች እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጐበኘና እህል እንደ ሰጣቸው በሰማች ጊዜ፣ ሁለቱን ምራቶቿን ይዛ ወደ አገሯ ለመመለስ ከዚያ ተነሣች።

የኖረችበትን ስፍራ ትታ ከሁለቱ ምራቶቿ ጋር ወደ ይሁዳ ምድር የሚመልሳቸውን መንገድ ይዘው ጒዞአቸውን ቀጠሉ።

ከዚያም ኑኃሚን ሁለቱን ምራቶቿን እንዲህ አለቻቸው፤ “እያንዳንዳችሁ ወደ እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ፤ ለሞቱ ባሎቻችሁና ለእኔ በጎ ነገር እንዳደረጋችሁ፣ ለእናንተም እግዚአብሔር እንደዚሁ ያድርግላችሁ፤ እያንዳንዳችሁ በምታገቡት ባል ቤት፣ እግዚአብሔር ያሳርፋችሁ።” ከዚያም ሳመቻቸው፤ እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤ ቀጥለውም፣ “አይሆንም! ከአንቺ ጋር ተመልሰን ወደ ወገኖችሽ እንሄዳለን” አሏት።

ኑኃሚን ግን እንዲህ አለቻቸው፤ “ልጆቼ ሆይ፤ ወደየቤታችሁ ተመለሱ፤ ከእኔ ጋር ለምን ትሄዳላችሁ? ባል የሚሆኗችሁ ሌሎች ልጆች ከእንግዲህ የምወልድ ይመስላችኋልን? ወደየቤታችሁ ተመለሱ ልጆቼ፤ ሌላ ባል እንዳላገባ እጅግ አርጅቻለሁ፤ አሁንም ተስፋ አለኝ ብል፣ ዛሬ ማታ አግብቼ ከዚያም ልጆች ብወልድ፣ እስኪያድጉ ድረስ ትጠብቃላችሁን? እነርሱን በመጠበቅ እስከዚያ ሳታገቡ ትቈያላችሁን? ልጆቼ ሆይ፤ እንዲህ አይሆንም፤ ሁኔታው ከእናንተ ይልቅ ለእኔ እጅግ መራራ ነው፤ የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ተነሥቶአልና።”

እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንደ ገና አለቀሱ፤ ከዚያም ዖርፋ አማቷን ስማ ተሰናበተቻት፤ ሩት ግን ልትለያት ስላልፈለገች ተጠመጠመችባት።

ኑኃሚን መልሳ፣ “እነሆ የባልሽ ወንድም ሚስት ወደ ወገኖቿና ወደ አማልክቷ ተመልሳለች፤ አብረሻት ተመለሽ” አለቻት።

ሩት ግን እንዲህ አለች፤ “ተለይቼሽ እንድቀር ወይም እንድመለስ አትለማመኚኝ፤ ወደምትሄጂበት እሄዳለሁ፤ በምትኖሪበትም እኖራለሁ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ፤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል። በምትሞቺበት እሞታለሁ፤ እዚያው እቀበራለሁ። ከእንግዲህ ሞት ከሚለየን በቀር ብለይሽ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህም የከፋ ያድርግብኝ።” ሩት አብራት ለመሄድ መቍረጧን በተረዳች ጊዜ፣ ኑኃሚን መጐትጐቷን ተወች።

ከዚያም ሁለቱ ሴቶች እስከ ቤተ ልሔም ድረስ ተጓዙ፤ ቤተ ልሔም እንደ ደረሱም፣ በእነርሱ ምክንያት ከተማው በሙሉ ተተረማመሰ፤ ሴቶቹም፣ “ይህች ኑኃሚን ናትን?” በማለት ተገረሙ። እርሷም እንዲህ አለች፤ “ሁሉን የሚችል አምላክ ሕይወቴን እጅግ መራራ አድርጎታልና ማራ በሉኝ እንጂ፣ ኑኃሚን ብላችሁ አትጥሩኝ። በሙላት ወጣሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ባዶዬን መለሰኝ፤ እግዚአብሔር አስጨንቆኝ ፣ ሁሉን የሚችል አምላክ መከራ አምጥቶብኝ ሳለ እንዴት ኑኃሚን ብላችሁ ትጠሩኛላችሁ?” አለቻቸው።

ስለዚህ ኑኃሚን ከምራቷ ከሞዓባዊቷ ሩት ጋር በመሆን ከሞዓብ ተመለሰች፤ ቤተ ልሔም የደረሱትም የገብስ አዝመራ በሚሰበሰብበት ወቅት መጀመሪያ ላይ ነበር።



# ሩት 1

**ማጣቀሻዎች**
**ዘፀአት 6፥8፣ ዘኁልቍ 14፥8፣ ዘዳግም 23፥3-6፣ ያዕቆብ 4፥13-15**
የሩትን ማንነት፣ ህይወት እንዲሁም በወንጌል ውስጥ ስላላት ሚና በጥልቀት ለማጥናት ከዚህ በላይ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያንብቡ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልከቱ፤ ያሰላስሉ።

- ዳኞቹ በሚገዙበት ጊዜ እስራኤል ምን ትመስል ነበር? ህዝቡ በአጠቃላይ ውሳኔዎችን ያደረገው በምን ላይ ተመስርቶ ነው (መሳፍንት 21፥25)?

- ከአቤሜሌክ ጋር ይህን ተመሳሳይ የውሳኔ አደራረግ ሂደት እንዴት እናየዋለን? ወደ ሞዓብ መሄዳቸው ለእነሱ ትክክለኛ ምርጫ ነበር? ለምን?

- በዚህ የውጭ አገር ውስጥ ምን ዓይነት ፈተናዎች ሊገጥሟቸው ይችላሉ?

- ይህ ውሳኔ ለቤተሰቡ ምን ውጤት አስገኘ? በረሀብ ምክንያት መሄዳቸውን ከግምት በማስገባት (በጤና ምክንያት) ውሳኔያቸው ውጤታማ ነበር?

- ኑኃሚን ወደ እስራኤል ለመመለስ የወሰነችበት ምክንያት ምንድነው? ለመመለስ እንቅፋት የሆኑባት ነገሮች አሉ? መመለስ ለእርሷ ጥሩ ውሳኔ ነበር?

- በዚህ ክፍል ስለ ኑኃሚን ምን እንማራለን? ስለ ኦርፋስ?

- ኑኃሚን አሁንም በጌታ እንዳመናች የሚያሳዩ ምን ማስረጃዎች ማየት እንችላለን?

- ኑኃሚን ሩት እና ኦርፋ በሞዓብ እንዲቆዩ ሐሳብ ያቀረበችው ለምንድን ነው?

- የእግዚአብሔር እጅ በእውነት በኑኃሚን ላይ ተነሥቶአል ብላችሁ  ታስባላችሁ? ?

- የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ተነስቶአል ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? እንደዚያ ሲሰማን ምን ምላሽ መስጠት አለብን?

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

የነገሮችን መጥፎ ጎን ማየት የሰው ተፈጥሮ ነው። ኑኃሚን “ባዶ ሆና” እንደመጣች ትገልጻለች። ግን የቤተልሔም ሴቶች ሩትን ከሰባት ወንዶች ልጆች እንደምትበልጥባት ይነግሯታል (ሩት 4፥15)። የራሳችንን አመለካከቶች እና ስሜቶች እንመርምር። በሰው ወይም በእግዚአብሔር ላይ የተማረርን ወይም የተናደድን ከሆነ እነዚህን ስሜቶች ማብላላት፣ ማውጣት እና ማከም መቻል አለብን። እግዚአብሔርን እናማክረው፤ እንጠይቀው።

ናኦሚ ፍጹም አልነበረችም፣ ግን ህይወቷ እና ምሳሌዋ በሩት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ግልፅ ነው። ሩት በኑኃሚን ምክንየት ወደ እምነት መጣች። በዚህ ውስጥ አንድ ትምህርት አለ፣ እግዚአብሔር ፍጹም ያልሆኑ ኃጢአተኞችን እንኳ ሌሎችን ወደ ራሱ ለመሳብ ሊጠቀምባቸው ይችላል። በዚህ ላይ ለማሰላሰል ጊዜ እንውሰድ፤ ሕይወታችን፣ ምስክርነታችን ምንም እንኳን ፍጹም ወይም እንከን አልባ ባይሆን፣ ወደ ድነት የጠራንን ፍፁም አምላክን አሁንም ለሌሎች ሊያመላክት ይችላል።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት መለየት እንችላለን? በጣም አስፈላጊ እና ብዙ ጊዜ የምንሰማው ጥያቄ ነው። አቤሜሌክ እንዳደረገው ብዙ አማኞች ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደታቸው እግዚአብሔርን ይተዉታል። ያዕቆብ በያዕቆብ 4፥13-15 ላይ እንደገለጸው፥ ሰዎች ጌታን ለማማከርም ሆነ ፈቃዱን ለማረጋገጥ እንኳን ሳይሞክሩ ብዙ እቅድ ያወጣሉ። ስለዚህ የመጀመሪያው እርምጃ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ መፈለግ መሆን አለበት ማለት ነው። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትክክል ማወቅ ከፈለገ እግዚአብሔር ፍላጎቱን፣ ልቡን ሊያጋራን ወደኋላ አይልም። በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈለግ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው አምስት ነገሮችአሉ።

- **መጽሐፍ ቅዱስ**: የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?
- **ጸሎት**: ጸልየንበታል? እራሳችንን ለእግዚአብሄር እቅዶች እየሰጠን ነው ወይስ የራሳችንን እቅድ እንዲባርክ ብቻ እየጠየቅነው ነው?
- **ምክር**: ሌሎች እግዚአብሔርን የሚፈሩ አማኞችን አስተያየታቸውን ጠይቀናል? መጽሐፍ ቅዱስ በመካሮች ብዛት ውስጥ ድል እንዳለ ይነግረናል። ለመቀበል በሚከብድ ጊዜም እንኳ እግዚአብሔርን የሚወዱ፣ የሚፈሩ  አማኞች እውነትን ይሰጡናል።
- **ሁኔታዎች**: እግዚአብሔር ግልጽ በሆነ መንገድ “አይሆንም” እንዲሉ ሁኔታዎችን ወስኗል? ሁኔታዎች በአጠቃላይ እንደ አወንታዊ ወይም አሉታዊ አመላካች መታየት የለባቸውም፣ ግን በእውነት የእርሱን ፈቃድ ለሚፈልጉ አማኞች በሁኔታዎች ውስጥ እቅዱን፣ የጊዜ አካሄዱን ይገልጻል።
- **በክርስቶስ ውስጥ ነፃነት**: ከላይ ባሉት አራት አጠቃላይ መርሆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጥንቃቄ ከፈለግን ታዲያ እግዚአብሔር ወደ መራን መሄድ እንችላለን። ከልባችን የእርሱን ፈቃድ ፈልገን ከሆነ የሚወደን አባታችን ሊመራን፣ ሊረዳን፣ ሊያረጋጋን ይወዳል። በተሰጠን የልግጅነት ነፃነት ላይ አርፈን መቀጠል እንችላለን።

# አሰላስሎት



# ሩት 2

ኑኃሚን፤ ከአቤሜሌክ ጐሣ የሆነ ቦዔዝ የሚባል ባለጸጋ የባል ዘመድ ነበራት።

ሞዓባዊቷ ሩትም ኑኃሚንን፣ “በፊቱ ሞገስ አግኝቼ ቃርሚያ የሚያስቃርመኝ ሰው ባገኝ እስቲ ወደ እህል አዝመራው ልሂድ” አለቻት።

ኑኃሚንም፣ “ልጄ ሆይ፤ ይሁን ሂጂ” አለቻት። ስለዚህ እርሷም ወጣች፤ ከአጫጆች ኋላ ኋላ እየተከታተለችም ከአዝመራው ቦታ ትቃርም ጀመር፤ እንዳጋጣሚ ትቃርምበት የነበረው አዝመራ ከአቤሜሌክ ጐሣ የሆነው የቦዔዝ ነበር።

በዚሁ ጊዜ ቦዔዝ ከቤተ ልሔም መጣ፤ አጫጆቹንም፣ “ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን” ብሎ ሰላምታ ሰጣቸው።

እነርሱም፣ “ እግዚአብሔር ይባርክህ” ብለው መለሱለት። ከዚያም ቦዔዝ የአጫጆቹን አለቃ፣ “ይህች ወጣት ሴት የማን ናት?” ሲል ጠየቀው።

የአጫጆቹም አለቃ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ከኑኃሚን ጋር ከሞዓብ ምድር ተመልሳ የመጣች ሞዓባዊት ናት። እርሷም፣ ‘አጫጆቹን እየተከተልሁ በነዶው መካከል እንድቃርም እባክህ ፍቀድልኝ’ አለችኝ። ለጥቂት ጊዜ በመጠለያው ከማረፏ በስተቀር፣ ወደ አዝመራው ቦታ ገብታ ከጥዋት አንሥቶ እስካሁን ያለ ማቋረጥ ስትቃርም ቈይታለች።”

ስለዚህም ቦዔዝ ሩትን፣ “ልጄ ሆይ ስሚኝ፤ ከእንግዲህ ወደ ሌላ አዝመራ ሄደሽ አትቃርሚ፤ ከዚህም አትራቂ፤ ከሴቶች ልጆቼ ጋር እዚሁ ሁኚ። ወንዶቹ የሚያጭዱበትን ዕርሻ ልብ እያልሽ ልጃገረዶቹን ተከተዪ፤ ወንዶቹ እንዳያስቸግሩሽም አስጠንቅቄአቸዋለሁ፤ ውሃ ሲጠማሽ ደግሞ፣ እየሄድሽ ወንዶቹ ሞልተው ካስቀመጡት እንስራ ቀድተሽ ጠጪ።”

በዚህ ጊዜ ወደ መሬት ዝቅ ብላ እጅ ነሣችው። እርሷም፣ “ባይተዋር የሆንሁትን እኔን ታስበኝ ዘንድ በፊትህ ሞገስ ለማግኘት የበቃሁት እንዴት ነው?” አለችው።

ቦዔዝም መልሶ እንዲህ አላት፤ “ባልሽ ከሞተ ጀምሮ ለዐማትሽ ያደረግሽላትን ሁሉ፣

አባት እናትሽን እንዲሁም የተወለድሽበትን አገር ትተሽ ቀድሞ ከማታውቂው ሕዝብ ጋር ለመኖር እንዴት እንደመጣሽ ነግረውኛል። ስላደረግሽው ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋሽን ይክፈልሽ፤ በክንፉ ጥላ ሥር ለመጠለል የመጣሽበት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ብድራትሽን አትረፍርፎ ይመልስልሽ።

እርሷም መልሳ፣ “ጌታዬ ሆይ፤ ምንም እንኳ፣ ከሴት ሠራተኞችህ እንደ አንዷቱ መቈጠር የማይገባኝ ብሆንም፣ እንድጽናና አድርገኸኛል፤ እንዲሁም እኔን አገልጋይህን በመልካም ንግግር ደስ አሰኝተኸኛል፤ ስለዚህ ሞገስህ እንዳይለየኝ እለምንሃለሁ” አለችው።

በምሳ ሰዓት ቦዔዝ፣ “ወደዚህ ቀረብ በዪ፤ እንጀራም ወስደሽ በወይን ሆምጣጤው አጥቅሽ” አላት።

እርሷም ከአጫጆች አጠገብ እንደ ተቀመጠች፣ ቦዔዝ የተጠበሰ እሸት ሰጣት፤ የቻለችውንም ያህል በልታ ጥቂት ተረፋት። ለመቃረም ስትነሣም፣ ቦዔዝ ጐበዛዝቱን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፤ “በነዶው መካከል እንኳ ብትቃርም ክፉ አትናገሯት፤ ይልቁንም ከየታሰረው ነዶ ላይ ጥቂት ጥቂቱን ዘለላ እየመዘዛችሁ በመጣል እንድታነሣው ተዉላት፤ አታስቀይሟት።”

ስለዚህ ሩት እስኪመሽ ድረስ ከአዝመራው ላይ ቃረመች፤ ከዚያም የሰበሰበችውን ገብስ ወቃች፤ አንድ የኢፍ መስፈሪያም ያህል ሆነ። ያንንም ይዛ ወደ ከተማ ሄደች፤ አማቷም የሰበሰበችው ምን ያህል እንደሆነም አየች፤ እንዲሁም ሩት የሚበቃትን ያህል ከበላች በኋላ አስተርፋ የነበረውን አውጥታ ለእርሷ ሰጠቻት።

አማቷም፣ “ዛሬ የቃረምሽው ከየት ነው? የትስ ቦታ ስትሠሪ ዋልሽ? መልካም ነገር ያደረገልሽ ሰው የተባረከ ይሁን” አለቻት።

ከዚያም ሩት ስትሠራ ስለዋለችበት ስፍራ ባለቤት ለአማቷ ነገረቻት፤ እርሷም፣ “ዛሬ ስቃርም የዋልሁበት አዝመራ ባለቤት፣ ስሙ ቦዔዝ ይባላል” አለቻት።

ኑኃሚንም ምራቷን፣ “በጎነቱን ለሕያዋንም ሆነ ለሙታን ማድረጉን ያልተወ እግዚአብሔር ይባርከው” አለቻት፤

ቀጥላም፣ “ሰውየው እኮ የሥጋ ዘመዳችን ነው፤ የመቤዠት ግዴታ ካለባቸው ዘመዶቻችን አንዱ እርሱ ነው” አለቻት።

ከዚያም ሞዓባዊቷ ሩት፣ “ደግሞም፣ ‘እህሌን ሁሉ አጭደው እስኪጨርሱ ድረስ ከሠራተኞቼ አትለዪ! ብሎኛል” አለቻት።

ኑኃሚንም ምራቷን ሩትን፣ “የኔ ልጅ፤ እንዲህ ካልሽማ ከሴት ሠራተኞቹ ጋር አብሮ መሄድ ይሻልሻል፤ ወደ ሌላ ሰው አዝመራ ብትሄጂ ጕዳት ሊያገኝሽ ይችላልና” አለቻት። ስለዚህ የገብሱና የስንዴው አዝመራ ተሰብስቦ እስኪያበቃ ድረስ፣ ሩት የቦዔዝን ሴቶች ሠራተኞች ተጠግታ ቃረመች፣ ከአማቷም ጋር ኖረች።

# ሩት 2

**ማጣቀሻዎች**
**ዘሌዋውያን 19 19:9-10፤ ምሳሌ 10:4፤ ምሳሌ 13:4፤ 2 ምሳሌ 2:15፤ መክብብ 9:10፤ ኤፌሶን 5:19**

- በብሉይ ኪዳን ቃርሚያ መሰብሰብ ምን ማለት ነበር? (ዘሌዋውያን 19፡9-10)

- በተለምዶ የሚቃርሙ ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው? ይህ ሩትና ናኦሚ በህብረተሰbu ውስጥ ስለነበራቸው ቦታ ምን ይነግረናል?

- እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቃርሚያ የማድረግ ልማድን ለምን አቋቋመ?

- ሩት ይህንን ከባድ የመቃረም ሥራ ለመጀመር በራሷ ስለ ተነሳሳች ስለ እርሷ ማንነት ምን እንማራለን?

- በቦዔዝ መስክ ላይ መገኘቷ የአጋጣሚ ነገር ነው? ይህ ስለ እግዚአብሔር አቅርቦት ምን ያስተምረናል?

- በቁጥር 4 ላይ ለሠራተኞቹ ሰላምታ ከሚሰጥበት መንገድ ስለ ቦዔዝ ባሕርይ ምን ግንዛቤ ማግኘት እንችላለን? በዚህ ላይ ተመስርተው ብዙ አለቆች ከሠራተኞቻቸው ጋር ውይይት ወይም ንግግር እንዴት ሊጀምሩ ይችላሉ?

- በቁጥር 7 ውስጥ ስለ ሩት የሥራ ሥነ ምግባር ምን ማየት እንችላለን?

- ጥሩ ሰራተኛ ስለመሆን ከዚህ ምንባብ ምን ትምህርት እናገኛለን?

- ከዚህ ምንባብ ስለ ቦዔዝ ምን እንማራለን? ስለ ሩትስ ምን እንማራለን?

- ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግን በተመለከተ በቁጥር 12 ላይ ከቦዔዝ ምን እንማራለን?

- ቦዔዝ ሩትን በዚህ መንገድ እንዲይዛት (እንዲንከባከባት) ያነሳሳው ምን ይመስላችኋል?

- በጊዜው ከነበሩ ብዙ የእርሻ ባለቤቶች በንብረታቸው ላይ ቃርሚያ የሚወስዱ ሰዎችን ከሚይዙበት መንገድ ይልቅ ቦዔዝ ለሩት የተለየ አመለካከት የነበረው ይመስላችኋል?

- ቦዔዝ ሩትን ትልቅ ውለታ እንደዋለላት እንዲሰማት አደረጋት? በችሮታ ስለመስጠት ይህ ምን ያስተምረናል?

- የንግድ ሥራን እንዴት ማከናወን እንደሚቻል ምን ትምህርት እንማራለን? ቦዔዝ ሥራውን በተቻለ መጠን በጣም ትርፋማ በሆነ መንገድ ያከናውን ነበር?

- ከቦዔዝ ስለ መልካም፣ እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ወንድ ምን ማየት እንችላለን? (በሚቀጥሉት ምዕራፎችም ይህን እያስተዋልን)

**ማጣቀሻዎች**
ምሳሌ 19:17፣ ያዕቆብ 1:27፣ የሐዋርያት ስራ 20:35፣ ምሳሌ 11:24-25፣ የማቴዎስ ወንጌል 10:42፣ ኤፌሶን 4:29፣ ቈላስይስ 4:6

- ሩት በዚያን ቀን ምን ያህል ሠርታ/ደክማ ሊሆን ይችላል?

- ኑኃሚን አንድ ሰው ሩትን እንዳስተዋለት ለምን አሰበች?

- ኑኃሚን በዚህ ክፍል ውስጥ እንዴት ለእግዚአብሄር ያላት አመለካከት ሲቀየር ማየት እንጀምራለን? ከዚህ በፊት መራራ ነበረች፣ አሁን ግን የእግዚአብሔርን ቸርነት እየተገነዘበች ነው። ለምን? እግዚአብሔር ተለውጧል? እግዚአብሔር ካልተለወጠ ታዲያ በምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 2 መካከል ምን ተለውጧል?

- ይህ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ያስተምረናል?

- በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር እጅ በእኛ ላይ እንደከበደ ሆኖ ከተሰማን ታዲያ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

- ሩት ምዕራፍ 2ን በአንድ ቃል ማጠቃለል ከተፈለገ የትኛውን ቃል እንመርጣለን? በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥስ?

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

ሩት እና ኑኃሚን ወደ ምድሪቱ ተመልሰዋል። ሩት እያደረገች ያለችው የመጀመሪያ ነገር ለመቃረም ፈቃደኛ ሆና መሄድ ነው። አንድ ሰው መጥቶ እንዲያድናት ወይም እንዲያገለግላት በዙሪያዋ ካሉ ሰዎች አትጠብቅም። ሩት መደረግ ያለበትን ተመለከተች እና አደረገች። ባይመችም እንኳን መደረግ ያለበትን የምንመለከት እና ከዚያ እርምጃዎችን የምንወስድ ሰዎች መሆን አለብን። ይህ ተግባራዊ ሊሆንባቸው የሚችሉባቸውን የሕይወታችንን ክፍሎች እናስብ።

ሩት ከጧት እስከ ማታ ትሠራ ነበር፤ በቁጥር 7ትም ላይ እንደገና ሩት በጣም ትጉ እንደሆነች እናያለን። ቀኑን ሙሉ የምትሠራው በአጭር እረፍት ብቻ ነበር። በትምህርት ቤትም ሆነ በስራም ሆነ በአገልግሎት፣ እንዴት እና መቼ ማረፍ እንዳለብን ለማወቅ ጥበብ ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ነው። እኔ ምን ዓይነት ሠራተኛ ነኝ ብለው ያስባሉ? ስለ እረፍት ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግረው ያውቃሉ?

ቦዔዝ የእግዚአብሔርን ሰው አስደናቂ ባሕርያትን በጥሩ ሁኔታ ተላብሶ እናያለን። በሕይወትዎ ውስጥ ስላሉ ወንዶች (ባል ፣ ወንድም ፣ አባት ፣ ወዘተ) ሲጸልዩ የሚከተሉትን ይመልከቱ።

- የቦዔዝ ንግግር በልቡ ውስጥ ያለውን ያሳያል። ከሩትና ከሠራተኞቹ ጋር ባደረገው ንግግር ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ይጠቅሳል፣ ያስታውሳል። (ማጣቀሻ: የማቴዎስ ወንጌል 12:34)
- ቦዔዝ ቸር ተግባቢ ነው፤ ቃላቶቹ በጨው የተቀመሙ ናቸው፣ ለሚሰሙትም መልካም ስብዕናን ያሳያል። በተለይ ከቁጥር 11 እስከ 12 ያሉትን ቁጥሮች ልብ ይበሉ።
- ቦዔዝ አሳቢ ነው፤ ቦዔዝ ሩትን በፍቅር ይንከባከባል፣ ፍላጎቶቿን እና ምኞቶቿ ለማሟላት ይጥራል።
- ቦዔዝ ለጋስ ነው፤ ሰብሎቹን ለማከማቸት ወይም ከእርሻው ሊገኝ የሚችለውን ትርፍ ሁሉ ለማግኘት አይሞክርም፤ ግን በቸርነት ያለውን ያካፍላል።

# አሰላስሎት

# ሩት 3

ከዚህ በኋላ አማቷ ኑኃሚን ሩትን እንዲህ አለቻት፤ “ልጄ ሆይ፤ የሚመችሽን ቤትሰ እንድፈልግልሽ አይገባኝምን? ከሴቶች ሠራተኞቹ ጋር አብረሽ የነበርሽበት ቦዔዝ፣ ዘመዳችን አይደለምን? ዛሬ ማታ በዐውድማው ላይ ገብስ ያበራያል፤ ተጣጠቢ፤ ሽቶ ተቀቢ፤ እንዲሁም የክት ልብስሽን ልበሺ፤ ከዚያም ወደ ዐውድማው ውረጂ፤ ይሁን እንጂ በልቶና ጠጥቶ እስኪያበቃ ድረስ፣ እዚያ መሆንሽን እንዳያውቅ ይሁን። በተኛም ጊዜ፣ የሚተኛበትን ቦታ ልብ ብለሽ እዪና ሄደሽ እግሩን ገልጠሽ ተኚ፤ ከዚያም የምታደርገውን ራሱ ይነግርሻል።”

ሩትም፣ “ያልሽውን ሁሉ አደርጋለሁ” አለቻት። ስለዚህ ተነሥታ ወደ ዐውድማው ወረደች፤ አማቷ አድርጊ ያለቻትንም ሁሉ አደረገች።

ቦዔዝ በልቶ ጠጥቶ ከጨረሰና ደስም ከተሰኘ በኋላ፣ ራቅ ካለው የእህል ክምር አጠገብ ለመተኛት ሄደ። ሩት በቀስታ ከአጠገቡ ደረሰች፤ እግሩንም ገልጣ ተኛች። እኩለ ሌሊት ላይ ሰውዬውን አንዳች ነገር አስደነገጠው፤ ገልበጥ ሲልም አንዲት ሴት እግርጌው ተኝታ አገኘ።

እርሱም፣ “አንቺ ማነሽ?” ሲል ጠየቀ። እርሷም፣ “እኔ አገልጋይህ ሩት ነኝ፤ መቤዠት የሚገባህ ቅርብ የሥጋ ዘመድ አንተ ነህና ልብስህን ጣል አድርግብኝ” አለችው።

እርሱም መልሶ እንዲህ አላት፤ “ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር ይባርክሽ፤ ከዚህ በፊት ካደረግሽው ይልቅ የሁኑ በጎነትሽ ይበልጣል፤ ባለጠጋም ሆነ ድኻ፣ ወጣት ወንድ ፈልገሽ አልሄድሽምና። አሁንም ልጄ ሆይ፤ አትፍሪ፤ የምትጠይቂውን ሁሉ አደርግልሻለሁ፤ አንቺ ምግባረ መልካም ሴት መሆንሽንም የአገሬ ሰው ሁሉ ያውቀዋል። ምንም እንኳ እኔ ቅርብ የሥጋ ዘመድ መሆኔ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ከእኔ ይልቅ መቤዠት የሚገባው ቅርብ የሥጋ ዘመድ አለ። ከዚህ ዕደሪ፤ ሲነጋም ሰውየው ሊቤዥሽ ከፈለገ፣ መልካም ነው ይቤዥሽ፤ የማይፈልግ ከሆነ ግን በሕያው እግዚአብሔር እምላለሁ፤ እኔ እቤዥሻለሁ፤ እስኪነጋም ድረስ እዚሁ ተኚ።”

ስለዚህም ሩት እስኪነጋ ድረስ እግርጌው ተኛች፤ ዳሩ ግን ማንም ሰው ተለይቶ ሊታወቅ በማይችልበት ሰዓት ቀደም ብላ ተነሣች፤ እርሱም፣ “ሴት ወደዚህ ዐውድማ መምጣቷ እንዳይታወቅ” አላት። እንዲሁም፣ “በላይሽ የደረብሽውን ልብስ

አቅርቢልኝ፤ ዘርግተሽም ያዢው” አላት፤

ዘርግታ እንደ ያዘችም፤ ስድስት መስፈሪያ ገብስ ሰፍሮ አሸከማት፤ ከዚያም ወደ ከተማ ተመለሰች ።

ሩት ወደ አማቷ እንደ ተመለሰች፣ ኑኃሚን፣ “ልጄ ሆይ፤ የሄድሽበት ጉዳይ እንዴት ሆነ?” ብላ ጠየቀቻት።

ሩትም ቦዔዝ ያደረገላትን ሁሉ ነገረቻት፤ ቀጥላም፣ “ ‘ወደ አማትሽ ባዶ እጅሽን አትመለሺ’ በማለት ይህን ስድስት መስፈሪያ ገብስ ሰጠኝ” አለቻት።

ኑኃሚንም፣ “ልጄ ሆይ፤ የሚሆነውን ነገር እስክታውቂ ድረስ ታገሺ፤ ጉዳዩ ዛሬውኑ እልባት ካላገኘ ሰውየው አያርፍም” አለቻት።



# ሩት 3

- ኑኃሚን በሩት መልሶ ማግባት ላይ ተስፋ በቆረጠችበት ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ አመለካከቷ እንዴት ተለውጧል? አመለካከቷ ለምን ተለውጧል ብላችሁ ታስባላቹ?

- በዚህ ክፍል ውስጥ በኑኃሚን ውስጥ ምን አይነት ባህሪዎችን ማየት እንችላለን? ምን አይነት እቅድ ታወጣለች? ስለ እቅዷ ምን ማለት እንችላለን?

- ሩት ወደ ቦዔዝ ለመጠጋት ለምን ጨለማን መረጠች? ይህ ተገቢ ነውን ወይስ አይደለም?

- ዛሬ አንዲት ወጣት ሴት ለወንድ ፍላጎት እንዳላት ለማሳየት ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ይኖርባታልን? በእንደዚህ ዓይነት ዕቅድ ውስጥ ምን አይነት አደጋዎች አሉ?

- ከዚህ ክፍል ስለ ሩት ምን እንማራለን?

- ከቁጥር 7 በዚያን ጊዜ ስለነበረው ባህል ምን እንማራለን?

- ሩት በቁጥር 9 ላይ ለቦዔዝ ምን የተለየ ጥያቄ አቀረበች? ኑኃሚን ምን እንድትል እና እንድታረግ ነግራት ነበር?

- በቁጥር 10-13 ውስጥ ስለ ቦዔዝ ግንኙነት ምን ምልከታዎች ሊኖሩን ይችላሉ?

- ቦዔዝ ሩትን ይወዳት ነበር ብለን ማሰብ እንችላለን? ለምን?

- ለእሱ ፍላጎት እንዳላት በመግለጿ ደስተኛ ልንሆን እንችላለን?

- በቦዔዝ እና በሩት መካከል ሊኖር ስለሚችለው የዕድሜ ልዩነት በጽሁፉ ውስጥ ምልክቶች አሉ? ይህ በዛሬው አለም ውስጥ ቢተገበር ምን አይነት እይታ ይኖረናል?

- ቦዔዝን ስለ ሩት ምን አስደነቀው?

- ቦዔዝ በዚህ ክፍል ውስጥ ምን ዓይነት ውሳኔ አደረገ?

- “ቤዛ” ወይም “መቤዠት” የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? በሩት እና በቦዔዝ ታሪክ አውድ ውስጥ ምን አይነት ትርጉም አለው?

- ሩትና ናኦሚ ምን ዓይነት ግንኙነት አላቸው?

- ወጣት አማኞች ኑኃሚንን የመሰሉ መካሪዎች እንዲኖሯቸው ለምን አስፈላጊ ሆነ?

- አማካሪዎች ወጣት ባለትዳሮችን ለመጠበቅ እና ተጠያቂ እንዲሆኑ እንዴት ሊረዱ ይችላሉ?

- ኑኃሚን በአንድ ቃል በሩት ቁጥር 18 ላይ ለሩት የተሰጠችውን ምክር እናጠቃልል። (ፍንጭ: ትዕግስት)

- በዚያን ጊዜ ሩት ምን ተሰምቷት ሊሆን እንደሚችል ከዚህ ምን ማስተዋል እንችላለን?

- ኑኃሚን በቁጥር 18 ላይ የትኛውን የቦዔዝን ባህርይ ትጠቅሳለች?

- አንድ ላይ ግንኙነት ለመጀመር ለሚያስቡ ጥንዶች የትኛውን አጠቃላይ መርሆዎች ከዚህ ምንባብ ልንማር እንችላለን?

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

ኑኀሚን የአማካሪነት ሚናዋን ትወጣለች። ቲቶ 2፥3-5ን እንመልከት። ኑኀሚን ድክመቶች ነበሯት ሆኖም ግን አሁንም በጌታ ላይ እምነት እንዳላት እናያለን። በአንዳንድ መንገዶች የሩት መልካም ባህሪ ላስተማረቻት ለኑኀሚን ምስጋነ የሚያሰጥ ነው። ሩት በኑኀሚን እና በእርሷተጽዕኖ ምክንያት ስለ ጌታ አውቃ ነበር፤ እናም እሱን ለመከተል ቆርጣ ተነስታለች። በህይወታችን ውስጥ መካሪ አለን? ከሌለን እግዚአብሔር ታማኝ መካሪዎች እንዲያዘጋጅልን እንጠይቀው። መካሪዎች ካሉን ደግሞ ስለ እነርሱ እና ከእነርሱ ጋር ስላለን ቁርኙት እንፀልውይ።

ቦዔዝ በሌሊት ሩትን እግሩ ስር ሲያገኛት ደንግጧል ግን አልረገመም። ይልቁን ሩት መሆኗን ካወቀ በኋላ ከአፋ የወጡት የመጀመሪያ ቃላት “ጌታ ይባርክሽ” የሚሉት ናቸው። ስንደናገጥ ወይም ጫና ሲሰማን ምን ምላሽ እንሰጣለን? እርስዎስ ስለ ጌታ የመናገር እና በቃልዎ ሌሎችን የመባረክ ልማድ አለዎት?

የፍቅር ግንኙነት ለመጀመር ፍላጎት ካለን ምክር መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ማየት የምንፈልገውን ብቻ እናያለን። እግዚአብሔር ጥበብ የተሞሉ ምክሮችን በትሕትና እና በእርጋታ እንድንፈልግ ይፈልጋል። በዚህ መንገድ ስኬት አለ። ኑኀሚን ለሩት ያወጣችውን ዕቅድ በሕይወትዎ ውስጥ ቃል በቃል መኮረጅ ብልህነት አይደለም፤ ግን የእሷን ዘዴዎች ከግምት ውስጥ እናስገባ። ምን አጠቃላይ መርሆች አእርሷ መማር እንችላለን? ከስር ያሉትን እንመልከት

- ኑኀሚን በቦዔዝ ባሕርይ ላይ አንዳች ጥርጣሬ ቢኖርባት ለሩት የሰጠቻትን ምክር ባልሰጠች ነበር። በአሰቡት የፍቅር አቻ ባህሪ ላይ እንደዚህ ያለ እምነት አለዎት?
- በግል ወደ ቦዔዝ እንድትቀርብ በማድረግ ኑኀሚን  በእቅዷ ሊፈጠሩ ከሚችሉ ወሬዎች እና ሐሜቶች ሩትን ታድናታለች። በግንኙነትዎ ውስጥ አስተዋይነት ምን ሚና ይጫወታል?
- እቅዷ ቀጥተኛ ነበር። ኑኀሚን በሐቀኝነት እና በግልፅነት ታምናለች ልንል እንችላለን። ስለዚህ ምን ይሰማዎታል? ኩራት ወይም ትዕቢት በውስጥዎ አለ?
- እቅዷ በተቻለ መጠን በቦዔዝ ላይ ጫና ላለመፍጠር ይጥራል። ማጭበርበር የለበትም። እርስዎ ወይም አጋርዎ በግንኙነቱ ውስጥ ያልተገባ ተፅእኖ ለመፍጠር ይሞክራሉ?
- እቅዷ ሥጋዊ አይደለም፣ ሩትንም ቦዔዝን ለማታለል አልተጠቀመችባትም። በንግግሯ ውስጥ ምንም አይነት የስጋዊ ወይም ፍትወታዊ ፍንጭ የለውም። በዚህ የንፅህና ጉዳይ ላይ ግንኙነቱ ውስጥ ምን አይነት አቋም አለ?

# አሰላስሎት

# ሩት 4

ቦዔዝም ወደ ከተማዪቱ በር አደባባይ ወጥቶ ተቀመጠ፤ እርሱም የመቤዠት ቀድሚያ ያለው የቅርብ ዘመድ በመጣ ጊዜ፣ “ወዳጄ ሆይ፤ ወደዚህ ና፣ አጠገቤም ተቀመጥ” አለው፤ ስለዚህም ሰውየው ሄዶ ተቀመጠ።

ቦዔዝ ከከተማዪቱ ሽማግሌዎች ዐሥሩን ጠርቶ፣ “እዚህ ተቀመጡ” አላቸው፤ እነርሱም ተቀመጡ። ከዚያም የመቤዠት ቀድሚያ ያለውን ቅርብ የሥጋ ዘመድ እንዲህ አለው፤ “ከሞዓብ የተመለሰችው ኑኃሚን፣ የወንድማችንን የአቤሜሌክን ጢንጦ መሬት ልትሸጥ ነው። አንተም ይህንኑ ጉዳይ ማወቅ አለብህ ብዬ ስላሰብሁ፣ አሁን እዚህ በተቀመጡትና በሕዝቤም ሽማግሌዎች ፊት እንድትገዛው ላሳስብህ ወደድሁ፤ አሁንም ራስህ የምትቤዠው ከሆነ ልትቤዠው ትችላለህ፤ ለዚህ ከአንተ ቀድሚያ የሚኖረው የለም፤ ይህን የማታደርግ ከሆነ ግን ከአንተ ቀጥሎ የሚገባኝ ስለ ሆንሁ፣ ንገረኝና ልወቀው።” ሰውየውም “እኔ እቤዠዋለሁ” አለ።

ከዚያም ቦዔዝ፣ “እንግዲህ መሬቱን ከኑኃሚንና ከሞዓባዊቷ ከሩት ላይ በምትገዛበት ዕለት የሟቹን ስም በርስቱ ለማስጠራት ሚስቱንም አብረህ መውሰድ አለብህ” አለው።

ያም ቅርብ የሥጋ ዘመድ፣ “እንዲህ ከሆነማ የራሴን ርስት አደጋ ላይ ልጥል ስለምችል፣ እኔ ልቤዠው አልችልም፤ አንተው ራስህ ተቤዠው” አለው።

በጥንት ዘመን በእስራኤል የመቤዠትም ሆነ ንብረት የማስተላለፍ ጉዳይ የሚጸናው አንዱ ወገን ጫማውን አውልቆ ለሌላው ወገን ሲሰጠው ነው፤ በእስራኤል ዘንድ መሸጥም ሆነ መግዛት ሕጋዊነት የሚኖረው በዚህ ሁኔታ ነበር።

ቀድሚያ ያለው ቅርብ የሥጋ ዘመድም ቦዔዝን፣ “እንግዲህ አንተው ራስህ ግዛው” ብሎ ጫማውን አወለቀ።

ቦዔዝም ለሽማግሌዎቹና ለሕዝቡ ሁሉ እንዲህ አለ፤ “የአቤሜሌክን፣ የኬሌዎንንና የመሐሎንን ንብረት በሙሉ ከኑኃሚን ላይ ለመግዛቴ፣ በዛሬው ዕለት እናንተ ምስክሮች ናችሁ፤

እንዲሁም የሟቹ ስም ከወንድሞቹ መካከልና ከአገሩ ደጅ እንዳይጠፋ፣ የሟቹን ስም በርስቱ ላይ ለማስጠራት የመሐሎን ሚስት የነበረችው ሞዓባዊት ሩትን አግብቼአታለሁ፤ እናንተም ዛሬ ምስክሮች ናችሁ።” ከዚያም ሽማግሌዎቹና በከተማዪቱ በር አደባባይ የነበሩት ሁሉ እንዲህ አሉ፤ “እኛ ምስክሮች ነን፤ እግዚአብሔር ይህችን ወደ ቤትህ የምትገባውን ሴት፣ የእስራኤልን ቤት በአንድነት እንደሠሩ እንደ ራሔልና እንደ ልያ ያድርጋት፤ አንተም በኤፍራታ የበረታህ ሁን፤ ስምህም በቤተልሔም የተጠራ ይሁን። እግዚአብሔር ከዚህች ወጣት ሴት በሚሰጥህ ዘር አማካይነት፣ ቤተ ሰብህን ትዕማር ለይሁዳ እንደ ወለደችው እንደ ፋሬስ ቤተ ሰብ ያድርገው።”

**የዳዊት የትውልድ ሐረግ**

ስለዚህ ቦዔዝ ሩትን ወሰዳት፤ ሚስቱም ሆነች። ከዚያም ወደ እርሷ ገባ፤ እግዚአብሔር እንድትፀንስ አደረጋት፤ ወንድ ልጅም ወለደች። ሴቶቹም ኑኃሚንን እንዲህ አሏት፤ “ዛሬ የሚቤዥ ቅርብ የሥጋ ዘመድ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ፤ በመላው እስራኤልም ስሙ ይግነን። ልጁ ሕይወትሽን ያድሳታል፤ በእርጅና ዘመንሽም ይጦርሻል፤ የምትወድሽና ከሰባት ወንዶች ልጆች የምትበልጥብሽ ምራትሽ ወልዳዋለችና።”

ከዚያም ኑኃሚን ሕፃኑን ተቀብላ ታቀፈችው፤ ሞግዚትም ሆነችው። ጎረቤቶቿ የሆኑ ሴቶችም፣ “ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት” አሉ። ስሙንም ኢዮቤድ ብለው ጠሩት፤ እርሱም የዳዊት አባት የሆነው የእሴይ አባት ነበር።

እንግዲህ የፋሬስ ቤተ ሰብ ትውልድ ይህ ነው፦

ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤
ኤስሮምም አራምን ወለደ፤
አራምም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፤
ነአሶን ሰልሞንን ወለደ፤
ሰልሞንም ቦዔዝን ወለደ፤
ቦዔዝም ኢዮቤድን ወለደ፤
ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፤
እሴይም ዳዊትን ወለደ።

Selah



# ሩት 4

- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ቦዔዝ ባህሪዎች ምን እናስተውላለን?

- ቦዔዝ ዘመዱን የት ተገናኘ? በግል ሳይሆን በከተማይቱ በር ለምን ተገናኘው?

- ምንም እንኳን ይህ ዘመድ ቦዔዝ የፈለገውን ነገር ከማግኘት ሊቀናቀነው የሚችል ቢሆንም፣ ቦዔዝ እንዴት አድርጎ አስተናገደው? እንዴትስ አነጋገረው?

- ቦዔዝ የከተማዋን ሽማግሌዎች ለምን ጠራቸው ብላችሁ ታስባላቹ? ከዚህ ምን ትምህርት እናገኛለን?

- በዘመናችን ባሉ የፍቅር ግንኙነቶች ላይ ሊተገበሩ የሚችሉ ከቦዔዝ የምንማራቸው እሴቶች አሉ?

- ስለ መግባቦት (communication) ምን አይነት መርሆች ልንማር እንችላለን?

- በቦዔዝ ዘመድ ውስጥ የትኞቹን ባህሪዎች እናያለን?

- እርሻውን ሊቤዠው ፈቃደኛ የሆነው ለምን ይመስልዎታል? ለምን ሩትንስ ለመቤዠት ፈቃደኛ ያልሆነ ይመስላችኋል?

- ይህ ዘመድ በህይወቱ ምን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ነበሩ ብለው ያስባሉ? እርሱን እና ቦዔዝን እናመሳስል፡፡

- ከእርሱ ህይወት እና ሁኔታ ምን ልንማር እንችላለን?

- ከምዕራፍ 1 ሲነፃፀር የኑኃሚን ሁኔታ እንዴት ተቀየረ? አመለካከቷስ እንዴት ተለውጧል?

- በምዕራፍ 1 ለመመለስ ከወሰነች ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር አቅርቦት በምን መልኩ እንዴት በራላት?

- በምዕራፍ 1፥21 ላይ አምላክ “ባዶ ሆና” እንደመለሳት ትናገራለች። እሷ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በነበረች ጊዜ እንኳን በእውነቱ ባዶ ነበረች?

- የሩትን ህይወት ሞዓብ ከነበረው እና በምዕራፍ 4 መጨረሻ በእስራኤል ካለው ስናነፃፅር ምን እናገኛለን? ነገሮች ለእሷ እንዴት ተለውጠዋል?

- ሩት ከእኛ ጋር የምትመሳሰለው በምን መንገድ ነው?

- በሁለቱ ግንኙነት ውስጥ አስጀማሪው ቦዔዝ ነው ወይስ ሩት?

# የአሰላሰሉት ጥያቄዎች

- የኑኃሚን ሕይወት በሕይወት ውስጥ ከባድ ውሳኔዎች ውስጥ እግዚአብሔርን ስለ ማስቀደም ምን ያስተምረናል?
- ካነበብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በሕይወት ውስጥ ከባድ ፈተናን ወይም ከባድ መከራን እንዴት መግጠም እንዳለብን ምን ልንማርእንችላለን?
- ራሳችንን ስንጠይቅ፡ ባዶነት በሚሰማን ጊዜ ራሳችንን በምን ለመሙላት እንሞክራለን? በባዶነታችን ውስጥ ኢየሱስ ራሱን “የሕይወት እንጀራ” እና “የሕይወት ውሀ” ብሎ መጥራቱን፡ ከእርሱም በልተን ጠጥተን ሁለተኛ እንደማንራብ፡ እንደማንጠማ ሲነግረን፡ ምን እናስባለን?
- ቦዔዝ ሩትን መቤዠቱ እየሱስ እኛን ስለ መቤዠቱ ምን አይነት ፍንጭ፡ ጥላ ይሰጣል? ቦዔዝ ከሩት ጋር ያለው ግንኙነት ክርስቶስ ከእኛ ጋር ካለው ግንኙነት በምን ይመሳሰላል?

# አሰላስሎት





# ጥበብ

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ
ያለመልማል፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ
ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።

መዝሙር 19:7

**ሁሉንም የሴላ ጥበብ ጥናቶች ለማግኘት**

www.selahethiopia.org/studies